**የኢትዮጵያ**
**ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)**
**ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)**

## መንግስት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የኑሮ ውድነት እና የኢንተርኔት ጉዳይ (እቀባ) ላይ የተፈጠረውን ጫና ላይ አፋጣኝ መፍትሔ ይስጥ!

የካቲት 30/2015ዓ.ም

**መግቢያ**

### የኑሮ ውድነት

በአዲስ አበባ ከተማ፣ በክልል ከተሞች እና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የኑሮ ውድነቱ እየተባባሰ የመጣ ሲሆን ይህም ማህበረሰቡ የቤት ኪራይ፣ የትራንስፖርት፣ የቁሳቁስ፣ የህክምና፣ የነዳጅና የትምህርት ወጪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ከመናራቸውም አልፎ የእለት ጉርሱን በአግባቡ እንዳያገኝ ተግዳሮት እየሆነበት ይገኛል፡፡ የኑሮ ውድነቱን ከሚያባብሱት ምክንያቶች አንዱ በተለያዩ አካባቢዎች በሚከሰቱት ግጭቶች ምክንያት የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ማለትም አርሶ አደሮች፣ ነጋዴዎች፣ ባለሀብቶች እንዲሁም የመንግስት ሰራተኞች ንብረታቸው በመውደሙና እንዲሁም ከአካባቢያቸው እንዲፈናቀሉ መደረጋቸው ሲሆን፤ ይህም አምራቹን እና መስራት የሚችለውን የማህበረሰብ ክፍል ስራ አጥ እና እርዳታ ፈላጊ እንዲሆን ማድረጉ፣ በተለያዩ አካባቢዎች እየተከሰተ ያለው ድርቅ እርዳታ የሚፈልጉ የማህበረሰብ ክፍሎችን በመጨመሩና ተመጣጣኝ የሆነ የምግብ እህል አቅርቦት እንዳይኖር ማድረጉ፣ በሌላ በኩል በአማራ፣ በኦሮምያና ሌሎችም ክልሎች የስንዴ እና ጤፍ አምራች የሆነ አርሶ አደር ያመረተውን ምርት በቀጥታ ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ ማህበረሰብ እንዲቀርብ ከማድረግ ይልቅ መንግስት ባስቀመጠው የዋጋ ተመን መሰረት ለማህበሮች እንዲሸጡ መደረጉ በዚህም ምክንያት አምራቹ አርሶ አደር ከሸማቹ ጋር በቀጥታ ባለመገናኘቱ እና በነጻ ገበያ ተጠቃሚ ባለመሆኑ በማምረት ሂደቱ የሚያወጣቸውን ወጪዎች ማለትም ማዳበሪያና ዘር የገዛበትን ለመሸፈን እንኳን በቂ ባለመሆኑ ያመረተውን እህል ለገበያ ባለማውጣቱ በቂ የሆነ የእህል አቅርቦት ችግር እንዲፈጠርና ማህበረሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እህል መግዛት እንዳይችሉ እያደረጋቸው መሆኑን እና ከላይ እንደተጠቀሰው የቤት ኪራይን፣ ትራንስፖርትን፣ የህክምና ወጪ፣ ቁሳቁስ፣ ነዳጅ ወዘተ በመሆኑ የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ ያደረገና ዜጎች ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በሌላ በኩል ከእህል አቅርቦት ችግር በተጨማሪ ከውጭ የሚገቡ እቃዎች ላይ የዋጋ ጭማሪ መደረጉ፣ የገበያ ስርዓት መዛባቱ ይህም ማለት ለገበያ የሚቀርቡት እቃዎችም ሆነ ሸቀጣ ሸቀጦች በተመጣጠነ መልኩ እኩል ተደራሽ አለመሆናቸው የኑሮ ውድነቱን እንዳባባሰው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማህበር ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ ገልጿል፡፡ በተጨማሪም የነዳጅ፣የህክምና፣ የትምህርት ቤት ክፍያ፣የቤት ኪራይ፣ ሸቀጣ ሸቀጥ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎቶች ላይ በየጊዜው እየተደረገ ያለው የዋጋ ጭማሪ የኑሮ ውድነቱን እያባባሰ የመጣ ጉዳይ መሆኑን ኢሰመጉ ተረድቷል፡፡

### የኢንተርኔት መዘጋት

ከየካቲት 2 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ቴሌግራም፣ ፌስቡክ እንዲሁም ሌሎች የትስስር ገፆች ላይ መንግስት ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ የገደበ ሲሆን አሁንም ይህ ገደብ እንደቀጠለ ይገኛል ይህም ሰዎች መረጃ የማግኘት፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ገደብ የሚጥልና የሚጋፋ ከመሆኑም በተጨማሪ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ እንደሚገኝ፤ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት መንግስት በኢንተርኔት ግንኙነት የጣለው ገደብ ሚዲያዎች ስራቸውን በአግባቡ ለህዝብ ተደራሽ እንዳያደርጉ እንቅፋት እየፈጠረ በመሆኑ ገደቡ ሊነሳ ይገባል የሚል መግለጫ ያወጣ ቢሆንም እስከአሁን ገደቡ ቀጥሎ ይገኛል፡፡ ተጠቃሚዎችም ገበያ ላይ በተገኘ በማንኛውም ቨርችዋል ፕራይቬት ኔትወርክ (VPN) ለመጠቀም በመገደዳቸው ምክንያት የመረጃዎችን ደህንነት ጉዳይ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ እንዲገኝ

አድርጎታል፡፡ ይህም መረጃን ለ3ተኛ ወገን አሳልፎ የመስጠት ስጋትን የሚያስከትልና በአጠቃላይ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ የቻለ ሲሆን፣

## ተያያዥ የህግ ድንጋጌ

የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 25 (1) ማንኛውም ሰው ለራሱ እና ለቤተሰቡ ጤና እና ደህንነት በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብት አለው, ይህም ምግብ, ልብስ, መኖሪያ ቤት እና ህክምና እና አስፈላጊ ማህበራዊ አገልግሎቶች እና ሥራ አጥረት ሲከሰት ዋስትና የማግኘት መብት አለው፡፡ ሕመም፣ አካል ጉዳተኝነት፣ መበለትነት፣ እርጅና ወይም ሌላ የኑሮ እጦት ከእሱ ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ዋስትና እንደሚያገኝ በግልጽ ይደነግጋል፡፡በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና የባህል መብቶች ላይ ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 11(1) የአሁን ቃል ኪዳን ተዋዋይ ወገኖች እያንዳንዱ ሰው ለራሱ እና ለቤተሰቡ በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት፣ በቂ ምግብ፣ ልብስ እና መኖሪያ ቤት እና ቀጣይነት ያለው የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ያለውን መብት ይገነዘባሉ። በነጻ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ የአለም አቀፍ ትብብር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ አባል ሀገራት ይህንን መብት እውን ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስዱ ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 43 የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይ በተለይም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተሻሻለ የኑሮ ደረጃ የማግኘትና ዘላቂ ልማት የማግኘት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይህም የተሻሻለ የኑሮ ደረጃ ማለት በቂ ምግብ፣ መጠለያ፣ ውሃ፣ ትምህርትን ያካተተ ሲሆን ዜጎች በበቂ ሁኔታ የማግኘት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ መንግስት ምግብ፣ መጠለያ መሳሰሉትን በቀጥታ ማቅረብ ባይችልም ማህበረሰቡ በራሱ ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ የማመቻቸት ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም የኑሮ ውድነቱ ማህበረሰቡ የምግብ፣ መጠለያና የመሳሰሉትን እንዳያገኝ ተግዳሮት እየሆነበት በመሆኑ ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው አለማቀፍም ህጎች እንዲሁም በህገ መንግስቱ መሰረት መንግስት ላይ ግዴታ የሚጥል በመሆኑ መንግስት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ መብት አለው ይህ መብት ድንበር ሳይገድበው በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም ሚዲያ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሐሳብ የመፈለግ፣ የመቀበልና የማስተላለፍ ነፃነትን ይጨምራል።

## የኢሰመጉ ጥሪ ፤

- መንግስት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ለመጣው የኑሮ ውድነት በቂ ትኩረት በመስጠት እና ለኑሮ ውድነት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በማጣራት ዘላቂ መፍትሔ ይስጥ፣
- መንግስት በኑሮ ውድነትም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ለተፈናቀሉ ሰዎች በቂ ትኩረት በመስጠት የስራ እድል በማመቻቸት አምራች የሚሆኑበትን ሁኔታ ቢያመቻች፣
- የአማራ፣ ኦሮምያና ሌሎችም ክልሎች አርሶ አደሮች ከማህበረሰቡ ጋር በቀጥታ የሚገናኙበትን ሁኔታ በመዘርጋት የኑሮ ውድነቱን ማረጋጋት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ቢችሉ፣
- የሚመለከታቸው የህግ አካላት በዝቅተኛ የክፍያ መጠን ተመን (minimum wage) ላይ ህጎችን ቢያወጡ እና ተግባራዊ የሚደረግበትን ሁኔታ ቢመቻች፣
- መንግስት ለአርሶ አደሮች የዘርና የመዳበሪያ ድጎማ በማድረግ ገበሬው ምርታማ እንዲሆን ቢያደርግ፣
- መንግስት ምክንያቱን ለህዝብ ሳያሳውቅ የኢንተርኔት አገልግሎት ማቋረጡ ተገቢነት የሌለው ድርጊት እና መረጃ የማግኘት መብትን የሚጻረር በመሆኑ እንዲሁም ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ በመሆኑ የኢንተርኔት አገልግሎት ገደቡን እንዲያነሳ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ